ሙባእ/መግቢያ

በዓለም ላይ የራሳቸው ቋንቋ ካላቸው ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ የኢትዮጵያ መሠረተ ቋንቋ የነበረው ግእዝ ከነበረበት የብሔራዊ ቋንቋነት ዛሬ ጠፍተዋል ከሚባሉት ቋንቋዎች ተራ የተመደበ ቢሆንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የተወሰነ ይሁን እንጂ እስካሁን ተናጋሪ ያላጣና ነሥጽሑፋዊ ሀብትነቱ የላቀ ቋንቋ ነው፡፡ ግእዝ የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የሃይማኖት መረጃዎች የተጻፉበት ቋንቋ ነው፡፡ ግእዝ ከ፬ኛ-፲ኛው መ/ክ/ዘ በንግግር ቋንቋነት ያገለገለ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከ፲፫ኛ-፲፱ኛው መ/ክ/ዘ/ ድረስ በሥነ ጽሑፍ ቋንቋነት ከፍተኛ ቦታ ይዞ የነበረ ነው፡፡ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የጽሑፍ ቋንቋነት ሥፍራውን አማርኛ የተረከበው ቢሆንም አሁንም ድረስ በተወሰነ መልኩ ሲሠራበት ይስተዋላል፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መተካት ለግእዝ መዳከም በዐቢይ ምክንያትነት የሚጠቀስ ቢሆንም ፣ በአሁኑ ወቅት ለቋንቋው የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆንም የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም አካል ግእዝ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ሳይሆን የኢትዮጵያ ቅርስ መሆኑን ተገንዝቦ ቋንቋው በአዲስ መልክ እንዲያድግ ጥረት ቢደረግና የቋንቋ ምሁራንም ለእድገቱ አስተዋጽኦ ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም ውድቀቱ አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ስለሚነካ ነው፡፡

ምዕራፍ አንድ

፩.ልሳነ ሴም

ሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ በሥነ ልሳን የጥናት ዘርፍ መሠረት በአፍሮ እስያዊ ዐቢይ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር ይገኛል፡፡ አፍሮ እስያዊ ዐቢይ የቋንቋ ቤተሰብ በዓለም ከሚገኙት ዐሥራ አንድ ዐቢይ የቋንቋ ቤተሰቦች መካከል የሚመደብ ሲሆን፣ በምሥራቅ እና በሰሜን አፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ እና እንዲሁም በባሕረ ሰላጤው አካባቢ የሚነገሩ ስድስቱን ንኡሳን የቋንቋ ቤተሰቦች ማለትም ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ኦማዊ፣ ቻድ፣ በርበርና ኮፕቲክ ይዞ ይገኛል[1]፡፡

ሴማዊ ከስድስቱ ንኡሳን ቤተሰብ አንዱ ሲሆን፣ ‹ሴማዊ› ማለት የሴም ማለት ነው[2]፡ ፡ ሴም ማለት ደግሞ ሰላም ማለት ነው፡፡ ‹ሴማዊ› የሚለው ስያሜ በምዕራብ እስያ በሚኖሩ ወገኖች ማለትም በዐረቦች፣ አርመኖች፣ እስራኤላውያን (የዘር ሐረጋቸው ከመጽሐፍ ቅዱሱ ከኖኅ ልጅ ከሴም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንደሆነ ይታመናል) እና በሌሎች ሕዝቦች የሚነገሩ ቋንቋዎችን ያካትታል፡፡

ሴማዊ የሚለውን ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ጀርመናዊው የሥነ ልሳን ምሁር ስክሎዠር (A.L.Schlöcer) ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስን (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕ.፲፥፭-፴፩ እና ፲፩፥፲-፳፮) መሠረት በማድረግ በ፲፯፻፹፩ዓ.ም እ.አ.አ ነው፡፡ ሴማዊ ቋንቋዎች ከስክሎዠር በፊት ለብዙ ዘመናት የነበሩ ቢሆንም የተለየ ስያሜ አልተሰጣቸውም፤ ነገር ግን እንደ ሌሎቹ የእስያ ቋንቋዎች የምሥራቅ ቋንቋዎች (Orental languages) ተብለው ይጠሩ ነበር[3]፡፡

ቀደም ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሴም ቋንቋ መነሻውን ሜሶፖታሚያ[4] አድርጎ ወደ ሰሜንና ደቡብ እስያ ተስፋፍቷል፡፡ ከዚያም ከፍልስጥኤምና ሶርያ ሰሜን ምዕራብ በመነሣት ወደ ደቡብ የመንና ወደ ኢትዮጵያ ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን አፍሪካ እንደ ሞሮኮ በመሳሰሉት አገሮች ተስፋፍቷል፡፡ ሆኖም አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች ሴማዊ ቋንቋዎች

---


[1] የቅርብ ጊዜ ጥናቶች የአፍሮ እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ መገኛው ቦታ አፍሪካ ሲሆን፣ የመወለጃ ቦታውም ደቡባዊ ኢትዮጵያ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

[2] ሴም የሚለው ስም ሴመ ካለው ግስ የወጣ ቃል እንደሆነ የሚነገር ሲሆን፣ ሴመ ሾመ ሴም ሹም ማለት ነው፡፡ “እግዚአብሔር በሴም ድንኳን ለዘልዓለም ይኑር” ዘፍ.፰፥፳4

[3] *An Introdaction to the Comparative grammar of Sematic languages.p.3*


[4] ሜሶፖታሚያ ማለት በሁለት ወንዞች መካከል የሚገኝ መሬት ማለት ነው፡፡ ሜሶፖታሚያ (የዛሬዋ ኢራቅ) በባቢሎን ወንዞች በጤግሮስና ኤፍራጥስ መካከል የሚገኝ ቦታ ሲሆን የጥንታዊው ሴም የአካድያን ማእከል እንደነበረ ይታመናል።

ከጀሺ ዓመታት በፊት ከኢትዮጵያ ተነሥተው ወደ እስያ በመሄድ በአሶርና በሶርያ እንደተሰራጩ ያትታለ፡፡



፩.የሴማዊ ቋንቋዎች ቤተሰብ ምድብ

ሴማዊ ቋንቋ በመልክአ ምድራዊ ስርጭቱ ሲታይ ሰሜን ምሥራቅ ሴማዊ (ሜሶፖታሚያ) ሰሜን ምዕራብ ሴማዊ (ሲሪያ-ፓሌስታይን) እና ደቡብ ምዕራብ ሴማዊ (ዐረብያና ኢትዮጵያ) ተብሎ ይከፈላል፡፡




፪. Approximate distribution of Semitic language around 1 A.D.(ምንጭ-wekipddiya free Ensy-kolpidiya 2012)

ደቡብ ምዕራብ ሴማዊ፡-ሰሜን ዐረቢክን፣ ጥንታዊ ደቡብ ዐረብያን፣ አዲሱን ደቡብ ዐረብያንና ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች በሚቀራረቡበት ድምፀ ልሳናዊ ባሕርይ ሰሜናዊ ኢትዮ-ሴማዊ እና ደቡባዊ ኢትዮ-ሴማዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ[5]፡፡

ሰሜን ኢትዮ-ሴማዊ	ደቡብ ኢትዮ-ሴማዊ
ግእዝ	አማርኛ
ትግረ	አርጎብኛ
ትግርኛ	የጉራጌ ቋንቋዎች

[5] የኢትዮ-ሴማዊ መወለጃ ቦታ በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦች ይሰነዘራሉ፡፡ የኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋ ግንድ (Proto Ethio Semitic) የበለጸገው በደቡብ ኢትዮጵያ በጉራጌ ምድር ነው፡፡ ይኸውም በኢትዮጵያ ካሉት ፲፮ ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ሦስቱ ብቻ በሰሜን ሲገኙ ሌሎቹ የደቡብ ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች በጉራጌ ዞን ይገኛሉ፡፡ ሌላው የደቡብ ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ግንድ ለሰሜኑ አያት ነው የሚል ሲሆን፣ በአንጻሩ የኢትዮ-ሴሜዊ መወለጃ ሰሜን ኢትዮጵያ እንደሆነ ይገለጻል፡፡



፫. Approximate historical distribution of Semitic languages.(ምንጭ - wekipddiya free Ensy-kolpidiya 2012 G.C) **Geographic distribution: (መልክዓ ምድራዊ ስርጭት)** Middle East, North Africa, Northeast Africa and Malta.**Linguistic lassification**፡East Semitic (extinct)- ሰሜን ምሥራቅ ሴማዊ,Central/West Semitic- መካከለኛው/ሰሜን ምዕራብ ሴማዊ,South Semitic -ደቡብ ምዕራብ ሴማዊ፡፡

፩.፩ የግእዝ ቋንቋ ምንነት፣ አመጣጥና ዕድገት

ቋንቋ ስልጣኔ ከመምጣት ጋር በተያያዘ ከንግግር ቋንቋነት አልፎ የጽሑፍ ቋንቋ መሆን ችሏል፡፡ በዚህ መልኩ በዓለም ላይ የራሳቸው ቋንቋና ፊደል ወይም የጽሕፈት ሥርዓት ካላቸው ጥቂት ሀገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ይኸውም ከዛሬ ፳፮፻፶፬ ዐመት ገደማ ጀምሮ የራሷ የጽሕፈት ሥርዐትና ቋንቋ ያላት ስትሆን፣ የዚህም የጽሕፈት ሥርዓት ቀዳሚ ባለ አደራ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ይነገር የነበረው ጥንታዊው ቋንቋ ግእዝ ነው፡፡

ግእዝ ማለት ምን ማለት ነው ?

ግእዝ የሚለው ቃል በውስጡ በሚይዛቸው ፊደላት ምክንያት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔና ስያሜ ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡

ግእዝ የሚለው ስም ገአዘ ወይም ግእዘ ከሚለው ቀዳማዊ አንቀጽ (ሥርወ ቃል) የወጣ ሲሆን ትርጉሙም መጀመርያ፣ አንድ፣ አንደኛ፣ ማለት ነው።

- *አንድም ግእዝ ማለት ከሁሉ በፊት፣ ቀዳማዊ ማለት ነው።*
- *አንድም ግእዝ ማለት ሰመ ተዐውዶ (የመጠርያ ሰም)፣ የቋንቋ ወገን፣ ልዩ ክፍል ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 1948፡29 ፣ 294)።*

ግእዘ አዘነ፣ ተቆጣ፣ ተበሳጨ፣ ማለት ሲሆን፣ ግእዝ ማለት አመል ፀባይ፣ ልማድ፣ ወዘተ.።።

- *አንድም ግእዘ አ.ጋዘ፣ተማረ፣ቆጠረ ማለት ሲሆን፣ግእዝ ማለት መጀመሪያ፣ የፊደል ሰም፣ የዜማ[6] ሰም ነው።።*

ግዕዘ ተጓዘ፣ ተነሳ አዘገመ፣ ነጻ አወጣ ማለት ሲሆን፣ግዕዝ (ነባር ሰም) ሜማዊ፣ ቀዳማዊ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት ነው (በላይ መኩንን 2000፡335)።።

ከላይ እንደተገለጸው ግእዝ የሚለው ቃል በውስጡ በሚይዛቸው ድምፆች መቀያየር ምክንያት የተለያየ ትርጉም ይኖረዋል። ይህም ግዕዝ የሚለው ቃል በዐይኑ "ዐ" ሲጻፍ ነጻነት ማግኘትን፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መጓዝን፣ የጊዜ መለዋወጥን ሁሉ ያመለክታል።

ስለ ግእዝ ቋንቋ የጻፉና ጥናት ያካሄዱ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ምሁራን በርካታ ናቸው። ከውጭ ሀገር ምሁራን መካከል አባ ሰላማ (ፍሬምናጦስ)፣ ፀዱ ቅዱሳን፣ ሰላማ መተርጉም እና ሌሎችም በማጥናትና በመተርጎም አስተዋጽኦ አድርገዋል። በተጨማሪም ከፓ፯ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተነሱ ከውጭ ሀገር ምሁራን መካከል ሂዮብ ሉዶልፍ፣ አገስት ዲልማን፣ ቶማስ ላምዲን፣ ወልፍ ሌስሎው እና ሌሎችም ግእዝን በተመለከተ ጽፈዋል።

የቋንቋውን ሰዋስውና አመጣጥ ማጥናት የተጀመረው ከፓ፫ኛው መ/ክ/ዘ አንሥቶ ሲሆን፣ በፓ፭፻፲፫ ዓ/ም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር (እ.አ.አ) የጉተን መጽሐፍ (ሰዋስወ ግእዝ) የመጀመሪያው ሥራ ነው[7]። ይህን ተከትሎ በፓ፭፻፺፪ዓ/ም እ.አ.እ የታተመው ደግሞ የማሪያ ስቪቶሪ የግእዝ ሰዋስው ነው። ከላይ ከተጠቀሱት እትሞች የተሻለ "የመጀመሪያው" የግእዝ ሰዋስው የታተመው (Lexixcon Aethiopico-Latinum) **በፓ፮፻፵፩ዓ/ም እ.አ.እ በጀርመናዊው ሂዮብ ሉዶልፍ ነው። በተጨማሪም በፓ፮፻፶፰ የአማርኛ ሰዋስው አሳትሞአል። ጀርመናዊው አገስት ዲልማን** (Ethiopic Grammar) **በፓ፯፻፺፭ዓ/ም እ.አ.እ ያሳተመው የግእዝ መዝገበ ቃላት ከሁሉም እጅግ የተሻለ ነበር። ዎልፍ ሌስሎው የግእዝ መዝገበ ቃላት** (Conscience Dictionary of Ge'ez) **በፓ፱፻፹፯ዓ/ም እ.አ.እ ያዘጋጀ ሲሆን፣ ቶማስ ላምዲንም** (Introduction to Classical Ethiopic) **በፓ፱፻፹፰ዓ/ም እ.አ.አ ዘመናዊ የግእዝ ሰዋስው አዘጋጅቷል።**

ከሀገር ውስጥ ምሁራን የሆሄያቱን ጠቀሜታ፣ የሰዋስውን አገባብና መዝገበ ቃላት የጻፉ እነ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ፓ፱፻፴፭) ፣ ሊቀ ጎሩያን በላይ መኩንን (ሕያው ልሳን፣ ፳፻) ፣ ዓለማየሁ ሞገስ (ሰዋስወ ግእዝ፣ ፓ፱፻፺)፣ አሥረስ የኔሰው (ትቤ አክሱም መኑ አንተ፣ ፓ፱፻፺፩) ፣ ያሬድ ፋንታ (ፍኖተ ግእዝ ዘመናዊ፣ ፓ፱፻፹፯)፣ ዜና ማርቆስ እንዳለ (ጥንታዊ ግእዝ በዘመናዊ ዘዴ፣ ፓ፱፻፹፩)፣ ዶክተር አምሳሉ አክሊሉ (Ge'ez Text 2012)፣ **ፕሮፌሰር አየለ በከሪ** (Ethiopic, an African writing system : its history and principles 1997) ፣ **ደሴ ቀለብ (ትንሣኤ ግእዝ፣ ፳፻፪)፣ ዘርአ ዳዊት አድሃኖና (መርኖ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ ፣ፓ፱፻፲፩) የመሳሰሉት ይገኛሉ።።**


[6] **ግእዝ የዜማ አይነትም ነው።። (ግእዝ፣ ዕዝል ፣ ዓራራይ)**

[7] **የመጀመሪያው የግእዝ ሰዋስው በሮም በፓ፭፻፴፭ዓ/ም እ.አ.አ የታተመው የጀ. ወመር ሥራ እንደሆነ ይገለጻል።**

የግእዝ ቋንቋን የትመጣነት በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶች አሉ[8]። የመጀመርያው አመለካከት ግእዝ የደቡብ ሴማዊ ቋንቋ ሳይሆን በዐረብ ምድር የመጀመሪያዎቹ የአፍሪካ (የኩሻውያን) ቋንቋ ነው የሚል ሲሆን፣ ይህን ሀሳብ ከሚያራምዱት ሊቃውንት መካከል አስረስ የኔሰው (፲፱፻፷፯)፣ ዶ/ር ኃይሉ ሀብቱ (፲፱፻፹፯)፣ ፕ/ር አየለ በከሪ(፲፱፻፷፯)፣ የሩሲያ ምሁራን እነኢጎር. ዲያክኖፍትና ኤቢ. ዶጎፖልስኪ ይገኙበታል። ከሌሎች ቋንቋ ጋር በማነጻጸር ግእዝ ሴማዊ ቋንቋ እንደሆነ ከሚገልጹት ሊቃውንት መካከል ሊኦኔል ቤንደር፣ ኤመርቶን ይገኙበታል። የግእዝ ቋንቋ በኋላ የመጣ ነው ባይሉም ከላይኞቹ ምሁራን ለየት ባለ መልኩ በግንባር ቀደምትነቱ የሚያስቀምጡት ፕ/ር ባየ ይማም ዩሴፍ ግሪንበርግ፣ ደሴ ቀለብ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ "የካም-የሼም" መባሉ ቀርቶ ግእዝ በአፍሮ እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ የሚታይ (የሚገኝ) ልደቱና እድገቱን "ኢትዮጵያ" አድርጎ በዘመነ ባቢሎን ሊነገር የሚችል አለማቀፋዊና ጥንታዊ ሴማዊ ቋንቋ ነው ብለው ያምናሉ (ደሴ ፣2002÷4)። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም ይህን ሐሳብ ይጋራል። ከዚህ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ደግሞ ፕ/ር ጌታቸው ጎይሌ ሲሆኑ፣ ቋንቋው የሼም ቢሆንም የቋንቋው ተናጋሪዎች እነማን እንደሆኑ ማወቅ እንደሚቸግራቸው ይገልጻሉ።

ቀደም ያሉ ጥናቶች የሼም ህዝቦች ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣታቸው በፊት ከደቡብ እስያ ወደ ደቡብ ዐረብያ በመምጣት ይኖሩበት የነበረው ቦታ ሳባ፣ ግእዝ፣ ሐበሻና ሕምያር ይባሉ እንደ ነበር ያመለክታሉ። በተጠቀሱት ቦታዎች ይኖሩ የነበሩ የሼም ነገዶች በተለያየ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ጀመሩ። አግዓዝያን ግእዝ ከተባለው አገር ሲመጡ፣ ነገደ ሐበሻት ሐበሻ ተብሎ ከሚጠራው ቦታ የመጡ ናቸው። ሌላው ነገደ ሼም ሳባ ሲሆን፣ ሳባ ከተባለው ቦታ (አገር) በመምጣት ቀድመው ከመጡት ከአግዓዝያን ከሐበሻና ከጥንቱ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ጋር በባህል በቋንቋ ተስማምተው በአክሱም፣ በየሀና አካባቢዋ መኖር ጀመሩ። ሕምያር ከተባለው ቦታ የመጡት ደግሞ (ሕምራውያን) አማሮች ናቸው። የሳባ ቋንቋ ከአግዓዝያን፣ ከሐበሻና ከጥንቱ የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ባህልና ቋንቋ ተስማምቶ ግእዝን ወለደ። በ፮ኛው መ/ክ/ዘ ዓመተ ዓለም ገደማ በሳባ ቋንቋ ፊደል የተጻፈ በአክሱም፣ በአዶሊስ፣ በመጠራና (ኤርትራ) በመሳሰሉት በድንጋይ ተቀርፆ ይገኛል። ከ፩፻፱-፫፻፷፩ ዓ/ም ድረስ የሳባና የግእዝ ቋንቋዎች አብረው ይነገሩ ነበር። በዚህ ወቅት ፊደሉ የሳባ ቋንቋው የግእዝ ነበር። በ፫፻፱ ዓ/ም የሳባ ቋንቋ ቀርቶ ሙሉ በሙሉ በግእዝ ተተካ። ከዚህ በታች የምናየው ካርታ ከላይ የተገለጸውን ሐሳብ የሚደግፍና አካባቢዎችን የሚያሳይ ነው።

[8]ግእዝ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ቋንቋና የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ይነጋገርበት የነበረ ቋንቋ እንደሆነ ከሚገልጹት መካከል አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ጀርመናውያኑ የስነ ልሳን ሊቃውንት ሲዲ ጳውሎስና መአልም ዮሐንስ ይገኙበታል። መርሻ አለኸኝ ‹ግእዝ ትላት፣ ዛሬና ነገ› ። ገጽ ፣117.



፬.ይህ ካርታ ነገደ አግዓዝያን ከደቡብ ዐረብያ ተነስተው ወደ የኢትዮጵያ እንደገቡ በደቡብ ዐረብያ ይኖሩበት የነበረውን አገር ስም አምጥተው በየኢትዮጵያ እንደሰየሙ ጥንት ኢትዮጵያ የምትባለው አገር ማን እንደነበረች የሚያሳይ ነው። (ምንጭ፡- አክሊለ ብርሃን ፣ መጽሔተ ጥበብ፡ 1948.)

በሌላ በኩል ነገደ ሐበሻት በ፲ኛው ምእተ ዓለም ሳባ ከሚባል ደቡባዊ ዐረብ አውራጃ በመነሳት በባብል መንድብ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በአክሱም እና አካባቢዋ መኖር እንደ ጀመሩና ኢትዮጵያም በስማቸው አቢሲኒያ ተብላ እንድትጠራ እንዳደረጓት ይገለጻል። እንዲሁም ከሐበሻት በኃላ ወደኢትዮጵያ የገባው ነገደ ሴም አግዓዚ ሲሆን፣ የአግዓዝያንም ቋንቋ ሌሎች የሳባውያን ቋንቋ አድክሞ ጠንካራ ቋንቋ ለመሆን ቻለ። አግዓዝያንም ሀገራቸውን ብሔረ አግዓዚ አስብለው ቋንቋቸውን ግእዝ አሰኝተዋል[9]።

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያስረዱት ሴማዊ ቋንቋ በጥንታዊ ደቡብ ዐረብያ ከመገኘቱ በፊት በአፍሪካ ቀንድ ፱ሺህ ዓመት ቅድሚያ የነበረው ሲሆን፣ ነገደ ሴም ሆኑ የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች ከዐረብያ የመጡ ሳይሆኑ ኢትዮጵያ የነበሩ ናቸው። በተቃራኒው የሴም ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ ወደ የመንና የመሳሰሉት ሄደዋል። ኢትዮ ሴማዊ ብቻ ሳይሆኑ የሴማውያን መነሻ ቋንቋ (Proto-Semitic) እና የአፍሮ እስያ (Afro-Asiatic) የቋንቋ ቤተሰብ መፈጠሪያ ምንጫቸውን ኢትዮጵያ አድርገው ወደ መካከለኛው ምሥራቅና ወደመሳሰሉት ተሰራጭተዋል። በተጨማሪ ከደቡብ ዐረብያ የፈለሰ "ሐበሻ" የሚባል ነገድ የለም። በተቃራኒው በዘመነ አክሱም ሐበሾች በየመን ስለመስፈራቸው በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። የኢትዮጵያን ምድር በጥንት ዘመን ሀገሩ ፑንት፣ ሕዝቡ ሐበሻ ተብሎ የሚጠራውና የሚታወቀው በምድረ ግብጽ የፈርያን ሥርወ መንግሥት ታሪክ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው (ላጲሶ፣1982፡23)፣ ሀብተ ማርያም 1986፡45፣ 336-375)።

[9] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አግዓዝያን በ፲ሺህ ዓመተ ዓለም ወደኢትዮጵያ እንደመጡ ይገልጻሉ። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ፣ገጽ.12.

የግእዝ ቋንቋ የሀገሪቱ ዋነኛ ቋንቋ ሆኖ ከ፭፻ ዓ/ዓ እስከ ፲ኛው መ/ክ/ዘ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ገደማ አገልግሎት ሰጥቶአል፡፡ ከ፲ኛው መ/ክ/ዘ-፲፫ኛው መ/ክ/ዘ መካከል በነበረው ዘመን የመነጋገሪያ ቋንቋ መሆኑ ቢያበቃም፣ ከ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ በኋላ የጽሑፍ ቋንቋ በመሆን እስከ ፲፱ኛው መ/ክ/ዘ ድረስ ቀጥሏል፡፡ ቦታውን ለአማርኛ ቋንቋ ከለቀቀ በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተወሰነ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

ግእዝ ፫ሺህ ዘመን ያስቆጠረ ከመሆኑም በላይ፣ በዘመነ አክሱም ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ የነበረና ኢትዮጵያን በዓለም የሥነ ጽሑፍ መድረክ ያስተዋወቀ ቋንቋ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዕብራይስጥ፣ ግሪክና ላቲን ቀጥሎ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመበት ፬ኛ ቋንቋ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ ያልዳሰሰው የዕውቀት ዘርፍ የለም፡፡ ብዙ የትርጉም ሥራ ሠርቶበታል፤ መንፈሳዊ ድርሳናት ተደርሰውበታል፤ የሀገርና የሕዝብ ታሪኮች፣ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የፍልስፍና መጻሕፍት ተዘግበውበታል[10]፡፡

፩.፪. የግእዝ ቋንቋ መዳከም

ልሳነ ግእዝ ከ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ ጀምሮ በጽሑፍ ቋንቋነት ቢወሰንም በንግግርም ሆነ አዳዲስ ድምፆችን ለመፍጠር ያደረገው አስተዋጽኦ ዛሬም አለ፡፡ ከ፲፫ኛ- እስከ ፲፱ኛው መ/ክ/ዘ ድረስ ከፍተኛ ሚና ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ ከ፲፱ኛው መ/ክ/ዘ በኋላ ለግእዝ ትኩረት ባለመስጠትና ማንነትን በመዘንጋት ቋንቋው ሊዳከም ችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት ብዙ የጽሑፍ ቅርስ የያዘውን የግእዝ ቋንቋ ከማወቅ ይልቅ የውጭ ቋንቋ የማወቅ ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ ለግእዝ ቋንቋ መዳከም አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ቋንቋውን ከሃይማኖት ጋር አያይዞ በማየት ሊዳከም ችሏል፡፡ ግእዝ የኢትዮጵያ ቋንቋ መሆኑ ለዓለም አስመስክሮአል፡፡ ሆኖም በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያን የመወሰንና ከሃይማኖት ጋር የማገናኘቱ ጉዳይ ቋንቋው እንዲዳከም አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በዘመኑ ምሁራን በመጣ የአመለካከት ችግር ቋንቋው ሊዳከም እንደቻለ ይታመናል፡፡ ከ፲፱፻፱ እስከ ፲፱፻፷ዓ/ም "የደራስያን ጦርነት" የሚባለው የብዕር ፊልሚያ ነበር፡፡ በወቅቱ ምሁራኑ በሁለት ጎራ ተከፍለው በጽሑፍ መነቃቀፍ የጀመሩበት ወቅት ሲሆን፤ ዘመናውያኑ ምሁራን የግእዝ ዕውቀት የነበራቸውን ደብተሮች ሲሉአቸው፤ የግእዝ ዕውቀት ያላቸው ደግሞ ግእዝ የማያውቁትን የግእዝ መሀይሞች በማለት ይነቅፏቸው ነበር፡፡ በትውልድ ላይ ጫና ማሳደር የቻሉት ዘመናውያኑ ምሁራን በመሆናቸው ቋንቋው ትኩረት እንዲያጣና ትውልዱ የደብተራ ቋንቋ፣ የቄስ ትምህርት፣ የቄስ ቁጥር እያለ እንዲሸሽ አስተዋጽኦ አድርጓል[11]፡፡

ቋንቋ የአንድ ማኅበረሰብ አካል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ የተቆራኘው በብዙ መንገድ ከግእዝ ቋንቋ ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ከጊዜው ጋር የተጣጣመ ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ፣ በግእዝ የተጻፉ ጽሑፎችን ማስተዋወቅና ጥቅማቸውን ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

፩.፫. ግእዝ ከደቡብ ዐረብያ ቋንቋ ጋር ያለው ግንኙነት

ቀደም ባሉ ጥናቶች መሠረት ሳባዊ ቋንቋ በደቡብ ዐረብ (የመን) ይነገር የነበረ ቋንቋ ሲሆን፣ ፭፻፱ ፊደላት አሉት፡፡ ግእዝም ከሳባ ቋንቋ ፊደሉን እንደ ወሰደ ይታመናል[12]፡፡ ግእዝ ከ፭፻፱

---

[10] በላይ መኮንን፡፡ *ሕያው ልሳን፡ግእዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* ገጽ.፭።
ግእዝ ለኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች (ትግረ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣...)አባት እንደሆነ የሚያምኑ ምሁራን ቢኖሩም፣ ይህን ሐሳብ የማይቀበሉ ምሁራን ይገኛሉ። ምክንያቱም ለተጠቀሱት ቋንቋዎች መነሻ የጋራ አባት ቋንቋ (ፕሮቶ ኢትዮ-ሴማዊ) አለ ተብሎ ስለሚታመን ነው።

[11] ሊ.ኅ .በላይ መኮንን ፡፡ ሕያው ልሳን፡ግእዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ ገጽ.፲፪

[12] የግእዝ ፊደል ከሳባ ፊደል መምጣቱ ከመታመኑ በፊት የተለያየ መላምት ተሰንዝረዋል፡፡ አንደኛው የግእዝን ፊደል ያመጡት ነገደ ሐበሻት ናቸው የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ግእዝ ፊደሉን የወሰደው ከግሪክ ፊደል ነው የሚል ምላምት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሂንዲክ ከተባለ ከህንድ ፊደል የመጣ ነው የሚል ሐሳብ ነበር፡፡

የሳባ ፊደላት ፮ቱን ትቶ ፳፬ቱን ፊደላት ብቻ ወስዷል። ሁለት ፊደላትን (ጸ፣ ፐ) ደግሞ ከሌላ ቋንቋ (ከግሪክ ቋንቋ) በመውሰድ ቁጥሩን ወደ፳፮ ከፍ እንዲል አድርጓል። ግእዝ የተዋቸው ፮ቱ የሳባ ፊደላትና የወሰዳቸው ፳፬ቱ የሳባ ፊደላት የሚከተሉት ናቸው።

፩.፫.፩ ግእዝ ከሳባ የወሰዳቸው ፊደላት

የሳባ ፊደል	የግእዝ ፊደል	የሳባ ፊደል	የግእዝ ፊደል	ያልተወሰዱት የሳባ ፊደላት
𐩣	አ	𐩠	የ	𐩵 𐩸 𐩺 𐩱 𐩦
𐩨	በ	𐩭	ከ	
𐩲	ገ	𐩫	መ	
𐩤	ደ	𐩬	ነ	
𐩧	ሀ	𐩮	ሠ	
𐩡	ወ	𐩯	ዐ	
𐩢	ዘ	𐩪	ቀ	
𐩩	ሐ	𐩰	ፀ	
𐩥	ረ	𐩱	ፈ	
𐩳	ጠ	𐩦	ጸ	
𐩴	የ	𐩣	ለ	
𐩷	ተ	𐩵	ሰ	

የሳባ ፊደል የግእዝን መልክ እንዲይዝ ሲደረግ በቀጥታ እንዳለ አልተወሰደም። ብዙ ለውጦች በፊደላቱ ላይ ተካሂዷል። አንዳንድ ፊደላት አቅጣጫውን እንዲለውጡ ሲደረግ፣ ሌሎቹ ደግሞ ቅርፃቸውን እንዲቀይሩ ተደርጓል።

፩.	አቅጣጫቸውን የቀየሩ	፪.	ቅርፃቸውን የቀየሩ	
	𐩤 = ደ		𐩣 = አ	𐩦 (𐩷) = ጸ
	𐩩 = ሐ		𐩡 = ወ	𐩱 = ፈ
	𐩫 = መ		𐩪 = ቀ	𐩣 = ለ
	𐩮 = ሠ		𐩲 = ገ	
	𐩷 = ተ		𐩠 = የ	
	𐩥 = ረ		𐩭 = ከ	

በተጨማሪም የአንዳንድ ሆሄያት መጠን ከሌሎቹ ሆሄያት ጋር ሲነጻጸር ተመሳሳይነት የለውም፡ ለምሳሌ 𐩯 /ዐ/ እና𐩡 /ወ/ ከሌላው አንፃር ሲታዩ አነስተኛ ነበሩ። ከሁሉም ጎልተው የሚታዩ ሆሄዎች ደግሞ𐩷 /ተ/ እና𐩵/በ/ ነበሩ። የሌሎቹ ፊደላት መጠን ግን መካከለኛ ነበር። ሁሉም ፊደላት በመጠን እኩል እንዲሆን ተደርጓል። ሆኖም የቅርብ ጊዜ ጥናቶች ግእዝ ከሳባ ፊደል የተቀዳ ሳይሆን ቀዳሚነት ያለው ከጥንት ሂሮግሊፕስ በቀጥታ የወረደ መሆኑን በተቃራኒው ሳባ ከግእዝ ፊደል የተወረሰ እንደሆነ ያመለክታሉ። ይህን አስመልክቶ ፕሮፌሰር አየለ በከሪ (1997) በጥናታቸው የግእዝ ፊደል የደቡብ ዐረብያ ፊደል ከመገኘቱ በፊት በ፪ሺ ዓ/ዓ ቀድሞ መገኘቱንና አፍሪካዊ ፈጠራና ከጥንታዊ ግብጽ ፊደል (ሂሮግሊፕስ) ግንኙነት

ያለመሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪ ግእዝ ከሳብኛ ለመምጣቱ ማስረጃ የለም፡፡ ሳብኛው ውስጥ ግን የግእዝ ነገሮች አሉበት፤ የድንጋዮቹ ጽሑፍ በኢትዮጵያና በደቡብ ዐረብያ መካከል ባህላዊ ግንኙነት መኖሩን ያሳያል እንጂ ግእዝ ከሳብኛ መምጣቱን አያመለክትም የሚል ሐሳብ እየተሰነዘረ ነው፡፡

፩.፬. ግእዝ ከሜማዊ ቋንቋ ፊደላት ጋር ያለው ዝምድና

ፊደል የሚለው ቃል ፈደለ ፣ ጻፈ ካለው ግስ የተገኘ ሲሆን፣ ትርጉሙም ጻፈ ማለት ነው፡፡ ፊደል ማለትም ጽሕፈት፣ የነገርና የቃል ምልክት፣ መግለጫና ማስታወቂያ (የንግግርና የድምፅን ሥዕል የሚያሳይ) ማለት ነው፡፡

- አንድም ፊደል[13] ማለት ፊደለ፣ ጣፈ፣ ቆጠረ፣ ለየ፣ መረጠ ይላል፡፡ ፊደልም ከዚህ ይወጣል፡፡ ልዩ ምርጥ ማለት ነው፡፡

የግእዝ ፊደላት ትርጉም ሥዕላዊ መገለጫዎች እንደነበሩ ይታመናል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ፊደላት የድምፅ ለውጥ በማድረጋቸው ከዘመን ብዛት ትርጉማቸውና ሥዕላዊ መገለጫቸው በተወሰነ ደረጃ እንደ ተዛባ ይገለጻል፡፡ በሜማዊ ቋንቋ ባህል መሠረት እያንዳንዱ ሆሄ የሚጠራበት ስም ያለው ሲሆን፣ የብዙዎቹ ቋንቋ ሆሄያት ስም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ግእዝም ከሳባ፣ ከዕብራይስጥ፣ ከዐረብና ከፊንቅ ጋር ይመሳሰላል[14]፡፡ የፊደሉ ቅደም ተከተልም ከሜማዊ ቋንቋ ፊደላት ቅደም ተከተል ጋር ተመሳሳይነት /ተቀራራቢነት አለው፡፡

[13] ‹ፊደል (ፍዱል)-ጥቅም፣ ችሎታ፣ ዕውቀት፣ ፍልሰፍ፣ ማለት ነው፡፡ ግሱም ፈደለ-ረባ፣ ጠቀመ፣ ለየ፣ ይላል፡፡ አፈወርቅ ዘውዴ፡፡ *ሀገረ መጻሕፍት*፣ ገጽ.፱፱፡፡ ፊደል ማለት መጽሔተ አእምሮ ማለት ነው፤ ምክንያቱም ያለፊደል ምንም አይታወቅምና፣ የአእምሮ መገመቻ የምሥጢር መመልከቻ ማለት ነው፡፡ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (አቡነ መልከ ጸዴቅ)፡፡ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፣ ገጽ. ፲፯ ፡፡

[14] ዶክተር ለይኩን ብርሃኑ ግእዝ ቀዳሚነቱ በቋንቋ ብቻ ሳይሆን በአጻጻፉም የመጀመሪያ ነው፡፡ የዕብራይስጥ፣ የግሪክ፣ የሮማይስጥ ፊደላት የተቀዱት ከግእዝ ፊደል ነው፡፡ የዐረብኛ አኃዝ ተብለው የሚነገሩት ዐሥሩ ቁጥሮች በቀጥታ የተወሰዱት ከግእዝ ቁጥር ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ *በሃይማኖት ካባ የሚሠራ ደባ*፡፡ገጽ.48-53፡፡

ሳባ	ግእዝ	ዕብራይስጥ	ዐረብ	ሦርያ	ፊኒቂያን	ግሪክ
𐩱	አ------አሌፍ	א-------አሌፍ	ا------አልፍ	ܐ --------አሌፍ	𐤀	A
𐩲	በ፠----ቤት	ב--------ቤት	ب--------ባእ	ܒ ----------ቤት	𐤁	B
𐩳	ገ------ጋሜል	כ--------ገሜል	ج -------ጀም	ܓ-------ገሜል	𐤂	Δ
𐩴	ደ-----ድንት	ד------ዳለጥ	د -------ዳል	ܕ ------ዳለጥ	𐤃	E
𐩵	ሀ------ሆይ	ה---------ሂእ	ﻫ ------ሂእ	ܗ --------ሂእ	𐤄	ζ
𐩶	ወ-----ዋዌ	ו----------ዋው	ر --------ዋው	ܘ -------ዋው	𐤅	Z
𐩷	ዘ------ዛይ	ז---------ዛይን	ذ -------ዛይ	ܙ ------ዛይን	𐤆	H
𐩸	ሐ----ሐውት	ח---------ሔት	ح-- (ሐ)ኘእ	ܚ ------ሔት	𐤇	Θ
𐩹	ጠ-----ጠይት	ט----------ጤት	ط -------ጣእ	ܛ --------ጤት	𐤈	I
𐩺	ኀ-----ኀረም	י-----------የድ	ي ------ያእ	ܝ -------የድ	𐤉	K
𐩻	የ------የማን	ך----------ካፍ	ي -----ካፍ	ܟ ------ካፍ	𐤊	Λ
𐩼	ከ------ካፍ	ל--------ላሜድ	ل ------ላም	ܠ --------ላም	𐤋	M
𐩽	ለ------ላዊ	מם--------ሜም	م -----ሜም	ܡ --------ሜም	𐤌	N
𐩾	መ-----ማይ	ן----------ኑን	ن ------ኑን	ܢ ---------ኑን	𐤍	Ξ
𐩿	ነ-------ነሐስ	ס-----ሳምኬት	س--ሳምኬት	ܣ ----ሳምኬት	𐤎	O
𐪀	ሠ----ሠውት	ע---------ዐይን	ع --------ዔ	ܥ ---------ዔ	𐤏	Π
𐪁	ዐ------ዐይን	ף----------ፌእ	ف ------ፌ	ܦ ---------ፌ	𐤐	P
𐪂	ፈ------ፋፍ	ץצ---------ጻዴ	ص---ጻዴ	ܨ ---------ጻዴ	𐤑	Σ
𐪃	ጸ-------ጸደይ	ק----------ቆፍ	ق ------ቆፍ	ܩ -------ቆፍ	𐤒	ϕ
𐪄	ቀ-------ቆፍ	ר----------ሬሽ	ر --------ሸን	ܪ --------ሬሽ	𐤓	Ψ
𐪅	ረ-------ርእስ	ש----------ሸን	ش ------ሸን	ܫ ---------ሸን	𐤔	X
𐪆	ሰ-------እሳት	ת---------ታው	ت -----ታው	ܬ ---------ሸን	𐤕	Ω
𐪇	ተ-------ታው			ܠ ---------- ታው		

ከላይ እንደ ተገለጸው ብዙዎቹ የግእዝ ፊደላት ስም ከሌሎቹ ሜማዊ ፊደላት ስም ሲመሳሰሉ፣ የጥቂት ሆሄያት ስም እንደ (ለ፣ መ፣ ረ፣ ነ፣ የ፣ ሠ) የመሳሰሉት ትንሽ ለየት ያለ ነው። ይህም ፀኛ መ/ክ/ዘ ላይ በተደረገው የፊደላት ቅደም ተከተል ለውጥ ጋር ተያይዞ የተደረገ የስም ለውጥ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን፣ ለግእዝ ቋንቋ አጠራር እንዲመች ሆኖ በመለወጡ የሚከተለውን ስያሜ አግኝቷል[15]።

[15] **የፊደላት ስምና ትርጉም በሳባ፣ በግእዝ፣ በዕብራይስጥና ዐረብኛ የሚከተለውን ይመስላል።**

የ=የማን→ቀኝ መ=ማይ→ውሃ	ረ=ርእስ→ራስ ነ=ነሐስ→እባብ	ሠ=ሰውት→ራስ ባለ ሦስት ጣት ማለት ነው፤ ለ=ላዊ፣ ላውይ→ጠማማ ማለት ነው፤

፩.፭. በግእዝ ላይ የተደረገ መሠረታዊ ለውጥ

ግእዝ የዛሬውን መልክና ቅርፅ ከመያዙ በፊት በተለያዩ ለውጦች ውስጥ አልፎአል። ግእዝ ካደረጋቸው ለውጦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፩. የአጻጻፍ አቅጣጫ ለውጥ፤ ፪. የፊደላት ቅደም ተከተል ለውጥ፤ እና ፫. የአናባቢ አጻጻፍ ጥቆማ መዘጋጀት ናቸው።

፩.፭.፩ የአጻጻፍ አቅጣጫ ለውጥ

የግእዝ ፊደል ይጻፍ የነበረው እንደ ሌሎቹ ሴማዊ ቋንቋዎች (ሳባ፣ ዐረብኛ፣ ዕብራይስጥ) ከቀኝ ወደ ግራ የነበረ ሲሆን፣ የአጻጻፉም ዘይቤ “የበሬ እርሻ” (boustrophedon) ይመስላል። ይህም እንደሳባ አጻጻፍ የመጀመሪያውን መስመር ከቀኝ ወደግራ አድርጎ ፪ኛውን መስመር ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ይወስደው ነበር። ሆኖም በ፫፻፵ዓ/ም በዐፄ ኢዛና ዘመን እንደግሪክ ቋንቋ ከግራ ወደቀኝ እንዲሆን ተስተካክሎና አናባቢ ተዘጋጅቶለት የሀገሪቱ ብሔራዊ ቋንቋ ሆነ።

አ አሌፍ፡- በሬ (የቀንድ ከብት)።
በ ቤት፡- የቤት ሥዕል።
ገ ጋሜል፡-ግመል ረጂም አንገት ያለው።
ደ ድንት፡- መዝጊያ (ደጅ አፍ)።
ሀ ሆይ፡- በራፍ (በከፊል የተከፈተ አፍ)።
ወ ዋው፡- ወገል፣ የመስኮት ሥዕል (በአረቢኛም ክብ ነው)።
ዘ ዛይ፡- ጌጥ፣ ሽልማት።
ሐ ሐውት፡- ዓሣ (በግእዝ ሐመር ይባላል= መርከብ ማለት ነው)።
ጠ ጠይት፡- ሠናይ ሥን ትክክል ማለት ነው።
ጎ ጎረም፡- አንድ ክንፍ ያለው የተተወ ልዩ ማለት ነው።
የ የማን፡-ቀኝ እጅ (ወደ ቀኝ የታጠፈ) ማለት ነው።
ከ ካፍ፡- የከብት እግር (ከብት)።
ለ ላዊ፡- አንገቱ የጎበጠ (ጠማማ) ማለት ነው።
መ ሜም፡- ማይ፡- ፈሳሽ ውሀ የሚመስል ማለት ነው።
ነ ኑን፡- ነሐስ ሸቦ (የታጠፈ ሸቦ)።
ሠ ሠውት፡- እሸት (ችፍግ ብሎ የወጣ)።
ዐ ዐይን፡- የዐይን ሥዕል።
ፈ ፈ፣ፋፍ፡- የአፍ ሥዕል (የተከፈተ አፍ መስሎ ከምላስ ጋር ይታያል)።
ጸ ጸደይ፡- ፍሬ የተሸከመ ሰብል።
ቀ ቆፍ፡- ዓላማ፣ ጌጥ በትክክል የቆመ።
ረ ርእስ፡- ከላይ ቀና ብሎ ከራሱ ከበድ ያለ።
ሰ እሳት፡- ከወደ ራሱ የእሳት ነበልባል የሚመስል (የሰው ሥዕል)።
ተ ታው፡- ባለ ሁለት ክንፍ (መስቀል የሚመስል)።
ጸ ጸይት፡- (በይት) ቤት፡ የበ፣ ፈ፣ ፐ ዲቃላ ለካማዊ ቋንቋ የተዘጋጀ በግእዝ ብቻ የሚገኝ።
ፐ ፐ(ፒ)፡-የ/ፈ/ ጓደኛ ሲጠብቅ/ፐ/ ሲላላ/ፈ/ተብሎ ይነገራል። በዕብራይስጡም /ፈ/ ተብሎ ይነበባል፤ የ/ፐ/ድምፅ በአብዛኛው የሚገኘው በግሪክ ቋንቋ ነው። ግእዝም ድምፅን የተዋሰው ከግሪክ ፊደል ነው።



፩. የሳባ ቋንቋ ጽሑፍ የአጻጻፍ አቅጣጫ የመጀመሪያውን መስመር ከቀኝ ወደ ግራ አድርጎ ሁለተኛውን መስመር ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ይወስደዋል። ግእዝም የአጻጻፍ አቅጣጫውን ከመቀየሩ በፊት ከላይ እንደምናየው እንደሳባ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ከቀኝ ወደ ግራ ከዚያም ከግራ ወደ ቀኝ ይጻፍ ነበር።

፩.፩.፪ የፊደላት ቅደም ተከተል ለውጥ

የግእዝ ፊደል የዛሬውን ቅደም ተከተል ከመያዙ በፊት እንደ ሌሎቹ የሴም ቋንቋ ፊደላት ቅደም ተከተል ተመሳሳይና የፊደላቱም ቅደም ተከተል **አ በ ገ ደ**...የነበረውና ሲሆን፣ ለአጋዝ ያገለግሉ ነበር። ነገር ግን በ[፻፸፭ዓ/ም ቅደም ተከተላቸው **በ ሀ ለ ሐ መ**... ተለወጠ[16]። በለውጡ ሂደትም አንዳንድ ፊደላት ድምፃቸውን አጥተዋል። ለምሳሌ፦ኧ>አ ተለውጧል። በተጨማሪም የፊደላቱ ቅደም ተከተል ሲለወጥ ለአጋዝ ከማገልገል አቆሙና በሌላ አጋዝ ተተኩ። ከታች የሚታየው የፊደላቱ ቅደም ተከተል **አ በ ገ ደ**...ወደ **ሀ ለ ሐ መ**... ከመለወጡ በፊት የነበረውን ይዘት ነው።

አ	**በ**	**ገ**	**ደ**	**ሀ**	**ወ**	**ዘ**	**ሐ**	**ጠ**	**የ**	**ከ**	**ለ**	**መ**	**ነ**	**ሠ**	**ዐ**	**ፈ**	**ጸ**	**ቀ**	**ቈ**	**ኧ**
𐩠	𐩡	𐩢	𐩣	𐩤	𐩥	𐩦	𐩧	𐩨	𐩩	𐩪	𐩫	𐩬	𐩭	𐩮	𐩯	𐩰	𐩱	𐩲	𐩳	𐩴

ከላይ እንደ ተገለጸው የግእዝ ፊደል ቅደም ተከተል ሲቀየር ለቁጥሮቹም አዲስ ምልክት ተዘጋጀላቸው (𐩵 𐩶 𐩷 𐩸 𐩹 𐩺...)። አዲሶቹ የግእዝ ቁጥር ምልክቶች ከግሪክ ፊደላት እንደ ተወሰዱ በብዙ ምሁራን ዘንድ ይታመናል[17]። የግሪክ ፊደል 𐩻𐩸 ሲሆኑ ለግእዝ ቁጥር የሆኑት ግን 𐩵𐩻ቱ ብቻ ናቸው። እነርሱም ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የተገለጹት ናቸው።

𐩵	𐩶	𐩷	𐩸	𐩹	𐩺	𐩻	𐩼	𐩽	𐩾	𐩿	𐪀	𐪁	𐪂	𐪃	𐪄	𐪅
A	B	Γ	Δ	E	Z	H	Θ	I	Λ	N	M	K	Ξ	O	Π	Σ	P

[16] የፊደል ቅደም ተከተል በተመለከተም የ ሀ ለ ሐ መ... ተርታ አዲስ የመጣ ሳይሆን ጥንታዊ እንደ ነበረ እና የ"አ በ ገ ደ" ተራም ከሃይማኖታዊ ትምህርት ጋር ተያይዞ የመጣ እንደ ሆነ ይገመታል።

[17] አሁን እያገለገሉ ያሉት የግእዝ ቁጥሮች ፺ኛው መ/ክ/ዘ ላይ የተዘጋጁ ናቸው። እንደ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገላለጽ ከግሪክና ከግብፅ /ኮፕቲክ/ የተወሰዱ ሲሆኑ፣ 𐩻 ቁጥር ግን የግእዝ ሮ ነው። "፯" እና "፻" አኀዝ እንጂ ፊደል አይባሉም ፊደልነት ስለሌላቸው በፊደል ተራ አይጻፉም። *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*። ገጽ. ፲፯ ። "ሣ" እና "ሦ" ከኮፕቲክ ፊደል የተወሰዱ ናቸው "ሣ " በኮፕቲክ "ሸ "ሲሆን "ሦ" ደግሞ "ፈ" ነው ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

𐩵	𐩶	𐩷	𐩸	𐩹	𐩺	𐩻	𐩼	𐩽	𐩾	𐩿	𐪀	𐪁	𐪂	𐪃	𐪄	𐪅
A	B	Γ	Δ	E	Z	H	Θ	I	Λ	N	ሣ	ሦ	=	ሮ	Π	=	P

፩.፭.፫ የአናባቢ አጻጻፍ ጥቆማ ማዘጋጀት

የግእዝ ፊደል የዛሬውን ቅርፅ ከመያዙ በፊት ይጻፍ የነበረው በተነባቢ ብቻ ነበር። (ለምሳሌ፡- ግእዝ በተናባቢ ተጽፎ በመጠራ (ኤርትራ) ሐውልት ላይ ይገኛል። ዘሐወለተ ዘአግበረ አገዘ ለአበወሀ=ሲነበብ⇒ ዝ ኽውልት ዘአግበረ አገዘ ለአበዊሁ። በአሁኑ ግእዝ አነጋገር⇒ዝ ሐውልት ዘአግበረ አገዘ ለአበዊሁ። ፫ኛው መ/ክ/ዘ ላይ እንደ ተጻፈ ይታመናል)። ሆኖም በ፬ኛው መ /ክ/ ዘመን ተነባቢን ከአነባቢ ጋር መጻፍ ተጀመረ[18]። ይህም የግእዝ ፊደል ቅደም ተከተል ከአ በ ገ ደ... ወደ ሀ ለ ሐ መ...ከተቀየረ በኋላ ሲሆን፣ የአናባቢ ቅጥያን በማዘጋጀት ምናልባትም ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ=የሰላም አባት/ከሣቴ ብርሃን=ብርሃንን የፈነጠቀ) በወቅቱ ከነበረው ንጉሥ አፄ ኢዛና እና ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ለአንዱ ፊደል ሰባት ድምፆች እንዲኖሩት ሆኖ ተዘጋጀ። አናባቢዎቹም ኧ፣ ኡ፣ ኢ፣ ኣ፣ ኤ፣ እ፣ አ ናቸው። ሆኖም የተዘጋጁት የግእዝ አናባቢ ቅጥያዎች ተመሳሳይነት የላቸውም [19] (ለምሳሌ፡- ቦ፣ ሎ፣ ሞ፣ ሮ፣ ሪ፣ ዬ፣ ሚ፣ ጋ፣ ፋ፣ ሳ፣ ዬ፣ ፌ፣ ብ፣ ክ ፣ል...ወዘተ.)። ይህ ችግር ግን በግእዝ ብቻ ላይ ሳይሆን በሌሎች ቋንቋዎች ላይም ይስተዋላል።

በሌላ በኩል በጥንቱ የልሳነ ግእዝ ሥነ ድምፅ (ሀ፣ ኀ፣ ሐ፣ አ፣ ዐ፣ ወ፣ የ፣) የግእዝ ሆሄያት አናባቢ ሆነው መዘጋጀታቸው የሚጠቀስ ሲሆን፣ ከሌላው የግእዝ ሆሄያት ጋር በተናጠል እየተደመሩ እያንዳንዱ ፊደል የራሱን ድምፅ እንዲያሰማ ያደርጉት እንደ ነበር ይወሳል።

፩.፭.፬ የፊደል ተቀራራቢ ድምፅ መፈጠር

ግእዝ ፭፮ መሠረታዊ ፊደላት ሲኖሩት እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ድምፅ አለው። ይሁን እንጂ ካሉት ፭፮ ፊደላት መካከል ሦስት [ሀ፣ ሐ፣ ኀ]፣ ሁለት [ሠ፣ ሰ] ፣ ሁለት [አ፣ ዐ]፣ ሁለት [ፀ፣ ጸ] በተመሳሳይ ድምፅ ይገኛሉ[20]። እነዚህም በጊዜና በታሪክ ሂደት የመጀመሪያ ድምፃቸውን ለቀው ተመሳሳይ ድምፅ እንደያዙ ይታመናል። ለምሳሌ በግእዝ [ዐ፣ ሐ] የጉሮሮ ድምፆች ሲሆኑ [አ፣ ሀ] የማንቁርት ድምፆች ናቸው። [ሐ፣ ዐ] ነባር ግን ወደ ማንቁርት ድምፅ ተለውጠው እንደ [አ፣ ሀ] በመሆን ድምፅ ይሰጣሉ (አሁን ድምፃቸው በትግርኛ ቋንቋ ይገኛል)። በተጨማሪም የ"ሀ" ፊደል ድምፅ ተቀይሮ "ሃ" ድምፅን ይዟል። በዚህም ግእዝ ከሴማዊ ቋንቋ ልዩነት አመጣ። "ሠ" በግእዝ= ሸ" ነበር። በዕብራይስጥም "ሠ"= ሸ ነው።

እንደ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አገላለፅ አባ ሰላማ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ ስለ ነበር በግሪክ ቋንቋ "ሸ" ስለማይገኝ በዚያ ተፅእኖ "ሠ" ን ወደ "ሰ" ተለውጧል። አማርኛና ትግርኛ ግን ሌላ

---

[18] እንደ ፕ/ር አየለ በከሪ አገላለጽ በፊደል ገበታው ያሉት ርባታዎች (ከካዕብ እስከ ሳብዕ) የተፈጠሩት በዓፄ ኢዛና ዘመን ነው የሚል እምነት እስከ ቅርብ ጊዜ ነበር። ሆኖም፣ ወደ ኋላ የተገኙ ማስረጃዎች እንዳረጋገጡት በፊደል ገበታው ያሉት ርባታዎች ከአፄ ኢዛና ዘመን ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ በአንደኛው ክፍለ ዘመን የተፈጠሩ ናቸው የሚል መደምደሚያ ተይዟል። አዲስ አድማስ፣ ታኅሣሥ ፲፯/፳፻፫።

[19] የአናባቢ ምልክቶች የተዘበራረቁ መሆን ለማጥናት አስቸጋሪ ስላደረገው ወጥና ተመሳሳይ ድምፅ ሰጪ ምልክቶች ማለትም ለካዕቡ አንድ ዓይነት ለሣልሱ እስከ ሳብዑ ድረስ ለየቤታቸው አንድ ዓይነት የድምፅ ሰጪ ምልክቶች መኖር አለበት በሚልበ20ኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ በምሁራኑ ውሳኔ ላይ ተደርሶ፣ በፊደላቱ ላይም የቅርፅ ለውጥ ተደርጎባቸው ለማሳየት ተሞክሮ ነበር።

[20] እነዚህ ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ፊደላት በዐረብኛም የቅርፅና የትርጉም ልዩነት አላቸው።

- ግእዝ → ሀ ሐ ኀ ሠ ሰ አ ዐ ጸ ፀ
- ዐረብኛ → ﻫ ح خ ﺽ س ا ع ص ض

“ሸ” ፈጥረው እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ ፊደላት በግእዝ ድምፃቸው ቢጠፉም በቅርፅ፣ በትርጉም (በአጻጻፍ) ልዩነታቸውን እንደጠበቁ ይገኛሉ፡፡ **ለምሳሌ፡-** በግእዝ ፊደላቱ/ሆሂያቱ ያላቸው የትርጉም ልዩነት እንደሚከተለው ነው፡፡

ሰ፣ሠ	አ፣ዐ እና ፀ ፣ ጸ	(ሀ፣ሐ፡ኀ)
ሰ- ሰአለ=ለመነ ሠ-ሠዐለ=ሥዕል ሣለ ሰ-ሰረቀ=ሰረቀ→ለሌባ ሠ-ሠረቀ= ወጣ→ለፀሐይ	አ-አመት =ሴት አገልጋይ ዐ-ዓመት=ዘመን፣ ጊዜ	ሐ-መሐረ=ማረ፣ ይቅር አለ ሀ- መሀረ =አስተማረ ኀ- ኀለየ=ዘመረ፣ ዘፈነ ሐ- ሐለየ= አሰበ
	ፀ-ፀሐይ =ፀሐይ ጸ-ጸልኦት=ጸልኦት	

ሞክሼ ፊደላትን (ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸውን ፊደላት) በተመለከተ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የፊደል ማሻሻያ ተብሎ ጉዳዩ ሲነሣ ከቆየ በኃላ፣ በደርግ ዘመነ መንግሥት የቋንቋ አካዳሚ ጉባኤ ትርፍ የሚባሉ ፊደላት እንዲወገዱ ወስኖ ነበር፡፡ ሆኖም ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ከውሳኔዎቹ መካከል ጥቂቶቹ ቋንቋው ካለው ድምፅ ጋር ሲመዘን ትርፍ ሆሂያት አሉት፣ ሞክሼ ፊደላት ይቀነሱ የሚሉ ነበሩ[21]፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የቋንቋዎች አካዳሚ ክብረ ነገሥት (የተባለውን መጽሐፍ ከግእዝ ወደ አማርኛ) በአንድ ፊደል ያስተረጎመ ሲሆን፣ ሐዲስ ዐለማየሁም “ፍቅር እስከ መቃብር” የተባለውን ልብ ወለድ መጽሐፍ ከሞክሼ ፊደላት መካከል ከያንዳንዳቸው አንዱን በመምረጥ በ፲፱፻፺፱ ዓ/ም አሳትመዋል (አማረ፣1999፡11-12)፡፡

በርካታ ምሁራን በየወቅቱ በመነሳት በግእዝ ሆነ በአማርኛ ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱትን ፊደላት መቀነስ አላስፈላጊና የትርጉም መፋለስ እንደሚያመጣ አስገንዝበዋል[22]። በተጨማሪም ከታሪክና ከማንነት አኳያ ይዘነው ልንጓዝ ይገባል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በእርግጥ ፊደላቱን ለይቶ አለመጻፍ የምስጢር መፋለስ ያመጣል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ይህ ችግር ይስተዋላል፡፡

፩.፮ .የግእዝ ቋንቋ ባሕርያት ከሜማዊ ቋንቋዎች ጋር ሲነጻጸር

ግእዝ ከሌሎቹ ሜማዊ ቋንቋዎች ጋር ሲነጻጸር የተናባቢ ጥብቀት አመልካች (gemmination) እና የአናባቢ ድምፅ ቆይታ (Vowel length) ምልክት የለውም፡፡ የተነባቢ ጥብቀት አመልካች በተናባቢ ፊደላት ላይ አለመኖር በንባብ ጊዜ ችግር ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ **ይቀትል** ‘ይገላል’ ይህ ቃል ሲነበብ ምንም ምልክት ስለሌለው ሊላላ ይችላል፡፡ ነገር ግን በግእዝ የንባብ

---

[21] **ሐመር መጽሔት.ቁ.፷፣ ፭፻ ገጽ.፲፷።** ፭ኛው መ/ክ/ዘ መጀመሪያ አንስቶ ምሁራኑ በኢትዮጵያ ፊደላት ላይ ጥያቄ ሲያነሡ ቆይተዋል፡፡ የቀድሞዎቹ ምሁራን ያነሡት የነበረው ጥያቄ እንደ ዛሬው መቀምር (Computer) ባልነበረበት ሰዓት የአማርኛ መጻፊያ መሣሪያ (type writer) ለማሠራት የአማርኛ ፊደላት በጣም ብዙ በመሆናቸው አላስፈላጊ ናቸው ያሏቸውን ፊደላት መቀነስ ግዴታ ነው ብለው ይከራከሩ ነበር፡፡ የዘመኑ ምሁራን የሚያነሱአቸው ጥያቄዎች፡- ፩.የፊደላቱ ብዛት ከሚገባው በላይ በመንዛዛቱ በመማር ማስተማር ተግባር ላይ መሰላቸትንና መወሳሰብን አስከትሏል፡፡ ፪.ሞክሼ ፊደላት መኖራቸው በሥነ ጽሑፎቻችን ላይ የተዘበራረቀ የፊደላት አጠቃቀም እንዲከሰት አድርጓል፡፡ ፫.የአናባቢ ወይም የድምፅ ሰጪ ምልክቶች ወጥ አለመሆን ወይም የተዘበራረቁ መሆናቸው እነእርሱን በቀላሉ ለማጥናት እንዳይቻል አድርጓል የሚሉ ናቸው፡፡

[22] ሊቀ ካህናት ክንፉ ገብርኤል፣ ስለፊደላቱ ጥቅም ሲያስረዱ፡-ለምሳሌ ሀብት የሚለውን ቃል በብዙኃኑ “ኀ” ስንጽፈው “የወይን ጭማቂ” ማለት ነው። በሐመሩ “ሐ” ሐብት ብለን ከጻፍን “አመነዘረ” ማለት ነው። በሃሌታው “ሀ” ሀብት ብንል ደግሞ “ንብረት” ማለት ነው፡፡ ስለዚህም መቀነስ የለባቸውም ይላሉ። ዶክተር ኃይሉ ሀብቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም መምህር የፊደላቱን መቀነስ እንደማይስማሙ ገልጸው፣ እያንዳንዱ ፊደል ድምፅ ብቻ ሳይሆን የሚወክለው ምስጢርን አኃዝንም ነው። ቻይናዎች ለምሳሌ ፭፻ ፊደላት አሏቸው። ሆኖም በሳይንሱ በጣም ልቀው ሄደዋል። የፊደላቱ መብዛት እድገታቸውን አልገታውም በማለት ያስረዳሉ፡፡ *ሰምዐ-ጽድቅ ፣ነሐሴ ፩/፲፭፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ.፲፪።*

ባህል መሠረት ጠብቆ መነበብ አለበት። ሆኖም የጥብቀት ምልክት[23] ስለሌለው ጠብቆ ይነበብ አይነበብ ማወቅ አይቻልም።

የአናባቢ ድምፅ ቆይታ አንድ የአናባቢ ድምፅ በአንድ ቃል ውስጥ በተመሳሳይ ፊደል ላይ ቃሉ በሚነገርበት ጊዜ የሚያሳየው የድምፅ ቆይታን ይመለከታል። በግእዝ ቋንቋ አናባቢ የድምፅ ቆይታ ላይ የሚታየው ሁኔታ የቆይታ ድምፅ አመልካች ምልክት አለመኖርና በሳድስ የፊደል አናባቢ ድምፅ ዜሮ መሆን ነው[24]። ለምሳሌ **ትምህርት** የሚለው ቃል የመጀመሪያ ፊደል "ት" እና የመጨረሻው ፊደል "ት" በቅርፅ አንድ ዓይነት ሲሆኑ፣ የቆይታ ድምፃቸው ግን ይለያያል። የመጀመሪያው /ት/ ረዘም ያለ የድምፅ ቆይታ ሲኖረው፣ የመጨረሻው /ት/ ድምፅ አጭር ነው። በዚህ ምክንያት ልዩነቱን መረዳት ሊያዳግት ይችላል። ሌላው ሳድስ ድምፅ በመሐል ሲመጣ ድምፁ ዜሮ ስለሚሆን በቀላሉ መረዳት ሊያስቸግር ይችላል።

፩.፯. በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች

በጥንት ጊዜ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ይጻፉ የነበረው በዚያን ዘመን በአስተዳደር ወይም በጊዜው በነበሩት ኀያላን ሀገሮች ቋንቋ ነበር። የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በወቅቱ የነበረውን የአንድ ሀገር ሕዝብ ታሪክ፣ ባህል፣ ፖለቲካ ፣ ሃይማኖትና የኢኮኖሚ ደረጃ ሊገልጹ ይችላሉ። ስለዚህ ስለአንድ ሀገር ምንነት ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ይቻላል። በጥንት ጊዜ በድንጋይ ላይ ታሪካቸውን ይጽፉ ከነበሩት አገሮች መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ለዚህም በአክሱም ዘመነ መንግሥት ተጽፈው የተገኙ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ሕያዋን ምስክሮች ናቸው። በአክሱም ዘመን ተጽፈው የተገኙት የጽሑፍ ዐይነቶች በሦስት ቋንቋዎች ማለትም በሳባ፣ በግሪክና በግእዝ (በአብዛኛው ፬ኛው መ/ክ/ዘ/ በኢዛና ዘመነ መንግሥት) ነው።

በዘመኑ ከነበሩት የአክሱም ዘመን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች የተወሰኑት በግሪክ ቋንቋ የተጻፉበት ዐቢይ ምክንያት በወቅቱ ዓለም አቀፍ ቋንቋ በመሆኑ ሲሆን፣ በሳባ የተጻፈበት ምክንያት ደግሞ ልሳነ መንግሥት ስለሆነና ከግእዝ በፊት ይነገር የነበረ ቋንቋ በመሆኑ ነው። በግእዝ የተጻፈበት የህዝቡ መግባቢያ ስለነበረ ነው። ጀርመናዊው የሥነ ልሳን ምሁር ኢኖ ሊትማን የአክሱም ዘመን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በሦስት መንገድ ማለትም በእድሜ፣ በይዘትና በተጻፉበት ቋንቋ ከፍሎ ከአስቀመጣቸው በኋላ በ፲፬ ከፍሎአቸዋል። በዚህ መሠረት በድንጋይ ላይ ተጽፈው ከተገኙት ፲፬ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ውስጥ ሰባቱ በግእዝ ሲጻፉ፣ የተቀሩት ማለትም አክሱም ፩፣ ፪ (ጳንጠሌዎን ፬፣ ፪) ፣ ፫ (ደቀ መሃሪ)፣ ፭፣ ፮ እና ስምንት በግሪክና በሳባ ተጽፈዋል። በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከላይ እንደተጠቀሰው ሰባት ሲሆኑ፣ በዐይነትና በእድሜ ተከፍለው ከዚህ በታች የተገለጹት ናቸው።

- **<u>አክሱም ሰባት /፯/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ አናባቢ በሌለው የግእዝ ፊደል የተጻፈ ነው። አክሱም ሰባት የተጻፈበት ዘመን ፬ኛው መ/ክ/ዘ መጀመሪያ ላይ ነው። የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ መሠረቱን የጣለው በዚህ ላይ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ።
- **<u>አክሱም ዘጠኝ /፱/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ አራተኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ በግእዝ የተጻፈ ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ አናባቢ ምልክት የታየበት የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ነው።
- **<u>አክሱም ዐሥር /፲/</u>**፡-የዚህ ጽሑፍ እድሜ ከአክሱም ዘጠኝ ጋር ተመሳሳይነት አለው። አናባቢ ምልክቱም የተስተካከለና ለማንበብ የማያዳግት ነው። ንጉሥ ኢዛና ጠላቶቹን ድል አድርጎ ከማረከው ላይ ለአምላኩ ፱ሰዎችንና ፩፱ ከብቶችን መሥዋእት የሠዋበትን ታሪክ ይዟል።

---

[23] በዐረብኛ ቋንቋ የጥብቀት ምልክት አለው። سرر = ደረሰ = ሲላላ سرّ= ደረሰ =ሲጠብቅ

[24] በዐረብኛ የድምፅ ቆይታ የልዩነት ምልክት አለ።ለምሳሌ፡-

- አጭር ድምፅ ምልክት→ ት=تِ
- የረጅም የጥብቀት ምልክት→ ትት=تِّ

- **<u>አክሱም ዐሥራ አንድ /፲፩/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ አራተኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ ላይ የተጻፈ ነው፡ ፡ የሚገኘውም በጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ውስጥ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ጽሑፍና ለኢትዮጵያ ታሪክ ላቅ ያለ ዋጋ ያለው ኢዛና ክርስትናን መቀበሉን የሚያሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጎይል እንደሰጠው ይገልጻል፡፡
- **<u>አክሱም ዐሥራ ሁለት /፲፪/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ ከ፯ኛው እስከ ፲፪ኛው መ/ክ/ዘ እንደ ተጻፈ ይታመናል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሓፊ ከሌሎቹ ጋር ሲነጻጸር ደካማ ይመስላል፡፡ ጽሑፉ አልፎ አልፎ አናባቢ ምልክት ሲኖረው፣ የተቀረው ግን ያለ አናባቢ የተጻፈ ነው፡፡ ተጽፎ የተገኘው በአንድ ዙፋን (ድንጋይ) መደገፊያ ላይ ነው፡፡ የቃላት መለያ ሰረዝ (/) ቀርቶ ነጥብ (፡) ተተክቶ የታየበት ጽሑፍ ነው፡፡ ስለ ሐፃኒ ዳንኤል ጦርነትና ምርኮ ይገልፃል፡፡
- **<u>አክሱም ዐሥራ ሦስት /፲፫/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ ከ፯ኛ-፲፪ኛው መ/ክ/ዘ እንደ ተፃፈ ይታመናል፡፡ ምናልባት የአክሱም ፲፪ ጸሓፊ እንደ ጻፈው የሚገመት አጣጣሉ የማያምር የተበላሸና አናባቢ የሌለው ነው፡፡ ጽሑፉ ሐፃኒ ዳንኤል በወልቃይት ሕዝብ ላይ ያደረገውን ጦርነትና ምርኮ ይገልፃል፡፡
- **<u>አክሱም ዐሥራ አራት/ ፲፬/</u>**፡-ይህ ጽሑፍ ከ፰ኛው-፲፪ኛው መ/ክ/ዘ እንደተጻፈ ታመናል፡ ፡ አናባቢና ቅጥያ በሌለው ግእዝ የተጻፈ ቢሆንም፣ ድንጋዩ ስላልተጎዳ ለማንበብ አያዳግትም አጣጣሉም ያምራል፡፡ ጽሑፉ አንድ ንጉሥ ወደ አክሱም መጥቶ መንገሥ መፈለጉንና ያንጊዜ አክሱም በሌላ ገዥ ሥር መሆኗን ያመለክታል፡፡

በዘመነ አክሱም በግእዝ የተጻፉ የድንጋይ ላይ ጽሑፉ እነዚህ ብቻ አይደሉም በአንድና በሁለት መስመር የተጻፉ በብዛት ይገኛሉ፡፡

<u>በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች</u>



<u>ምልማድ ቀዳማይ</u>

<u>I-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ ባዶ ቦታውን በቃላት (በሐረግ) ሙላ፤</u>

፩. ሜማዊ የሚለውን ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው----------ይባላል፡፡

፪. ግእዝ ከ፲ኛው መ/ክ/ዘ እስከ፲፫ኛው መ/ክ/ዘ መካከል በነበረው ዘመን የመነጋገሪያ ቋንቋመሆኑ ቢያበቃም--------የጽሑፍ ቋንቋ በመሆን ቀጥሎአል፡፡

<u>II-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ በማንበብ ተስማሚውን መልስ (ማብራሪያ) ስጥ፤</u>

፩. አፍሮ እስያዊ ዐቢይ ቋንቋ ቤተሰብ በስሩ ስንት የቋንቋ ቤተሰቦች ይዞ ይገኛል ? ዘርዝር፡፡

፪. የግእዝ ቋንቋ የዛሬውን መልክና ቅርጽ ከመያዙ በፊት በተለያዩ ለውጦች ውስጥ አልፏአል፡፡ ለውጦቹ ምን ምን ናቸው ?

፫. በግእዝ ቋንቋ የምናየው የፊደል ድምፅ ድግግሞሽ እንዴት ሊከሰት ቻለ? ምክንያቱን ግለጹ።

፬. ለግእዝ ቋንቋ ስድስት አናባቢ ድምፆች መቼ ተዘጋጁ ? በማን?

፭. የግእዝ ቋንቋ ሊዳከም የቻለበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግለጹ።